# የወቅቱ ጀምላ የትብብር ጥያቄና የወደፊቷ ኢትዮጵያ
**ከእስከመቼ አዘጋጆች**
**ሐምሌ ፱ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.**

የ፳፻፪ ዓ. ም. “ምርጫ” ትልቁ ውጤት፤ በተቃዋሚ ወገን የተሠለፉትን ኃይሎች እንዲተባበሩ መንገድ መጥረጉ ነው። መንገዱንም በመከተል፤ የትብብር ጥሪዎች ድረገፆችን፣ የሬዲዮ ሥርጭቶችን፣ የፖልቶክ መወያያ ክፍሎችን አሙቀውታል። ይህ በእቅፍ አበባ የሚታጀብ እና እሰይ የሚባል ክስተት ነው። ተከትሎ መምጣት ያለበት ደግሞ፤ እሽ! መልካም! እስኪ ስለዚህ ትብብር ውይይት እናድርግ ነው። መቸም ትብብርን የመሰለ ድንቅ ነገር ሲመጣ የማይደሰት የለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ፤ እንደልማዱ፤ ድርጅቶችን ቀድሞ፤ “ተባበሩ ወይንም ተሠባበሩ” ካለ ከርሟል። ታዲያ ምን ውይይት ያስፈልጋል? መፈላለግና መተባበር ነው እንጅ!

ያገሬ አርሶ አደር፤ “እየተስተዋለ እንጅ” ይላል ቸኮል፣ ቸኮል ሲሉበትና የጉዞው አያያዝ አልጥምህ ሲለው። ከማንኛውም የፖለቲካ ነጥብ ይልቅ፤ ይኼን ያሁን ሰዓት፤ የትብብር ጥያቄ ልዩ የሚያደርገው ሀገራዊ ይዘቱ ነው። ይህ የአሁኑ የትብብር ጥሪ በግለ ሰብና በግለሰብ መካከል የሚደረግ ድርድር ወይንም በአንድ ድርጅትና በሌላ ድርጅት መካከል የሚደረስ ስምምነት አይደለም። ይህ የአሁኑ የትብብር ጥሪ የማንም ድርጅት የግል ጉዳይ አይደለም። የሁላችንም ጉዳይ ነው። ይህ የአሁኑ የትብብር ጥሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከገዢው ቡድን ጋር የሚደረገውን ፍልሚያና ውጤት ይወስናል። ይህ የአሁኑ የትብብር ጥሪ የወደፊቷን ኢትዮጵያ መልክና ይዘት ይወስናል። ይህ የአሁኑ የትብብር ጥሪ ከባድ፣ እጅ እግር የሚጠፍርና፣ ዳግም ዕድል የማይሠጥ ክስተት ነው።

ታዲያ የሰከነ ውይይት መቼ ይበዛበታል! አያችሁ፤ እስከዛሬ ታሪክ ለጋስ ሆኖ በተደጋጋሚ ያደለንን ብዙ አጋጣሚዎች በአግባቡ ሳንጠቀምባቸው፤ ያለፈውን የክፍለ ዘመን እኩሌታ አባክነነዋል። ይችኛዋ ቁልፍ ናት። በቁልፍነቷም በር ከፋችና ከንቻሪ ናት። ስለሆነችም፤ ለዚሁ ክስተት ትኩረታችንን ያኑ ያህል ክብደት ልንሰጠው ይገባል። እናም ከዚህ በመነሣት ነው ለውይይቱ ይረዳ ዘንድ ይኼንን መንደርደርያ ያቀረብነው።

ከሁሉ መቅደም ያለበት፤ ይህ የትብብር ጉዳይ የወደፊት ጉዳይ እንጅ የወደኋላ ጉዳይ አለመሆኑ ነው። ስለዚህ ትናንት እኔ እንዲህ ብየ ነበር ማለት ቦታ የለውም። በተጨማሪም፤ እስከዛሬ የተደረጉትን የግለሰቦችም ሆነ የድርጅቶችን ጥረት፤ በዛም አነሰም፣ ጠቀመም ጎዳም፣ የይስሙላም ሆነ የቅንነት፤ መኮነን አፍራሽ ነው። ባጭሩ እያንዳንዳችን፤ ሌሎችን ጥፋተኞች ማድረግ እናቁም። በሚያውቁት ሞክረዋል። በሚችሉት ታግለዋል። በመሠላቸው ተሣትፈዋል። ላለንበት ሁኔታ እያንዳንዳችን ተጠያቂዎች ነን። የሚበጀው ደግሞ የወደፊቱን ማሣመር ነው። ለዚህ ሥምረት ደግሞ አንድነታችን የግድ ነው። ተጨባጩ ሁኔታ ደግሞ ታሪክ እንደገና አሁንም ለጋስ ሆኖ ፊቱን ወደእኛ አዙሯል። ኢሕአዴግ፤ በፖለቲካው ምኅዳር፤ **“ብቻየን ነው ያለሁ። ከኔ ውጪ ያለ በሙሉ ጠላቴ ነው።”** ብሏል። ሠፈሩ እግዲህ ወይ ኢሕአዴግ አለያም የኢሕአዴግ ጠላት ሆነ ማለ ነው፤ በኢሕአዴግ ቋንቋ! በሕዝብ ቋንቋ ደግሞ፤ ወይ የሕዝብ አለያም የሕዝብ ጠላት ነው። ኢሕዴግ የሕዝብ ወዳጅ አለመሆኑን ነጋሪ አንሻም። እናም ሠፈር መካለሉ ተጠናቋል። እያንዳንዳችን የምንችለውን ማድረግ፤ ሌሎች የሚያበረክቱትን ማድነቅና፣ ባጠቃላይም የሌሎችን የተሣትፎ ደረጃ በመልካም ዓይን መመልከት እንቅስቃሴውን ያጠነክረዋል። በአንድነት የሚኖረን ቀና አመለካከት ከምናደርገው አስተዋፅኦ ሲደመር፤ እንቅስቃሴያችን ገች የለውም። ድሉ የኛ ነው። እንግዲህ እዚች ላይ የምንሰነቅረው ዋና ነጥብ አለ። ትብብሩ ጥሩ ነው። መፈላለጉ ይበል ያስብላል። በመተባበሪያ ነጥቦች ላይ ግን ወለም ዘለም የለም።

- **የሀገራችን አንድነት፣**
- **የሕግ የበላይነት፣**

- ትግሉ የኢትዮጵያዊያንና በኢትዮጵያዊያን መሆኑ፣
- ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ቀጥተኛ የምናደርገው ጉዟችን፣ እና
- የሕዝቡ የትግሉ ባለቤትነትና የበላይነት

ለድርድር የማይቀርቡ የእንቅስቃሴው ዓምድ ናቸው። እነዚህ ለምንም ነገር ፈቅ የማይሉ የትግላችን መሠረቶች ናቸው። እንቅስቃሴው ረጅምና በደረጃ የተከፋፈለ ነው። አንዱ በር ሲከፈት የሚቀጥለው ይዘጋጃል። አሁን ሀገር እናድን። ይህ የሀገር አድን እንቅስቃሴ፤ በትክክለኛ ሥርዓት ከተመራ፤ ከፍተኛ ኅብረተሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ ለውጥን ያስከትላል። በሂደቱም ለዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት የሆኑትንና የምንታገልላቸውን፤ የሕግ የበላይነት፣ የግለሰብ መብቶች፣ የትክክለኛ መንግሥታዊ ተቋማት መዋቀርና ተግባራዊ መሆን፣ እውነተኛ ነፃና ሕዝባዊ አመኔታ ያላቸው ምርጫዎች፣ አቅጣጫችን ይሆናል። እነዚህ እየተጠናከሩ ከሄዱ፤ ኅብረተሰብዓዊ የዕድገት ጉዟችን ወደኋላ የማይቀለበስበት ደረጃ እንገባለን። ይህን የሽግግር ወቅት ነው እንግዲህ ረጅምና በደረጃ የተከፋፈለ ነው ያልነው።

አጠቃላይ ጥቋሜውን እዚህ ላይ በመቋጨት፤ እስከመቼ፤ ኑ እኔን ተቀላቀሉ ሣይሆን፤ አዲስ ልምድ በመቅደድና ጋባዥነቱን ለናንተ በመሥጠት፤ በምትጠሩት የትብብር እንቅስቃሴ ልንመጣላችሁ ተዘጋጅተናል። በብሎግ ስፌር፤ ከሚጥሚጣ ገርልስ እስከ ትልልቅ ድርጅቶች፤ በፖለቲካው ሥምሪት ደግሞ ከግለሰብ እስከ ሥልጣን ተፎካካሪ ፓርቲዎች - በሰላማዊ መንገድ ሆነ በትጥቅ አመፅ ከተሠማሩት፤ ስትጠሩን ይዘን የምንቀርበው ከዚህ የሚከተሉትን ነው። እናንተም ይዛሁ የምትቀርቡትን ጨምረን ውይይቱን እናጧጡፋዋለን።

፩ኛ. የአሁኑ ትንቅንቅ፤ ኢትዮጵያዊነትን ያነገበ፣ የሕዝቡን ነፃነት ያስቀደመና፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ያለመ እንቅስቃሴ ባንድ በኩል፤ የዚህ ተፃራሪ የትግል መስመር በመሆን የቆመ በሌላ በኩል ነው፤

፪ኛ. ምንጊዜም ቢሆን የሕዝቡ ለትግሉና ለውጤቱ የበላይነትና ሙሉ ተሣታፊነት በአንደኛ ደረጃ የሚቀመጥ ነው፤

፫ኛ. የዚህ ወቅት ተልዕኮ ሕዝብን ማሰባሰብ፣ ሠልፍን ማጠናከር፣ እና ትክክለኛ አመራር መሥጠት እንጅ፤ አጋጣሚ ተገኘ ብሎ ፅናት የሌላቸውን ቁንፅል እርምጃዎችን በመሞከር ጥንካሬንና ጊዜን ማባከን አይደለም።

፬ኛ. ለትብብርና ሁሉን ለማቀፍ ሲባል፣ ቆራጥነት የጎደለው፣ ጭፍንና ዥዋዥዌ አጫዋች፣ ክፍት ሆኖ ማንም ባመቸው ሊጎትተው የሚችልና፣ የወደፊቷን ኢትዮጵያ አደጋ ላይ የሚጥል እንቅስቃሴ መወገድ አለበት፤

፭ኛ. ለአጭር ግኝት ሲባል፤ መሠረታዊ የሆነውን፤ ሁላችንን ያሰባሰበንን የሀገር ሕልውናና የሕዝባችንን የአንድነት ነፃነት በምንም መንገድ መበረዝ የለብንም፤

፮ኛ. የእንቅስቃሴው ግብ በግልፅ፤ በእንቅስቃሴው የሚተባበሩት ክፍሎች በዕውቅ፤ የእንቅስቃሴው የሂደት ዕቅድ በንጥር መቀመጥ አለበት፤

፯ኛ. የሚተባበሩት ክፍሎች፤ ግለሰቦችም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ በዚህ ሀገር የማዳን እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ተማምነው መግባት አለባቸው፤

፰ኛ. የሚተባበሩት ክፍሎች፤ የቅድሚያ ተግባራቸው ሀገር ማዳን ሆኖ፤ የግልና የድርጅት መርኅ ግብራቸውን፤ ለዚህ ከፍተኛ ተግባር፤ ተገዢ ማድረግ አለባቸው፤

፱ኛ. በሂደቱ ግለሰቦችና ድርጅቶች፤ ውይይቶችን በማድረግ፤ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ማጥበብና በመካከላቸው ውህደት መፍጠር ይችላሉ፤

፲ኛ. አንጋፋዎቹ የየድርጅቶች መሪዎቻችን የተከታዮቻቸው ወጣቶችን ሚና መገንዘብና እኒሁኑ ወጣቶች በእኩልነት ተቀብሎ፣ አሁኑኑ በመሪነት ማስቀመጥ አለባቸው፤ ትግሉ የዛሬና ለነገ እንጅ፤ የትናንትናና ለትናንትና አይደለምና፤

፲፩ኛ. ይኼን እንቅስቃሴ፤ ግለሰቦች፤ ለግል አጀንዳቸው ማራመጃ እንዳያደርጉት፤ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤ በተለይም ያሁኑን ወቅት የራስን የግል የሥልጣን ጥማት

ለማሟላትና ቂም በቀል ለመወጣት መሯሯጫ በማድረግ፤ ያልሆኑ እርምጃዎችን፤ የማይጣጣሙ አሰላለፎችንና፣ አደገኛ የውጭ ዕርዳታ መሠባሠቦችን ለማሟጠጥ የሚሯሯጡትን ከመካከላችን ማስወገድ ይገባል።

፲፪ኛ. በዚህ እንቅስቃሴና በሀገር አቀፉ የፖለቲካ ሥምሪት፤ ሀገር አቀፍ የፖለቲካ አጀንዳ ሣያነግቡ፤ በግልፅ የተቀመጠ አካባቢ ተኮር መርኅ ግብራቸውን በሥራ ላይ ለማዋል ቆርጠው የተነሡ የክልል የፖለቲካ ድርጅቶች ቦታ የላቸውም። ይህን በትብብር ሥም ለማስተናገድ መሞከር አድርባይነት ነው። በፖለቲካ አመለካከት ላይ የተመሠረተ ሀገር አቀፍ የፖለቲካ አጀንዳ እንዲይዙ ማበረታታቱ የቀሪዎቻችን ድጋፍ የሚጨመርበት ሲሆን፤ ፍላጎቱና ወሳኝነቱ የድርጅቶቹ ነው፤

፲፫ኛ. ይህ እንቅስቃሴ በምንም መልኩ፤ በሥልጣን ላይ ካለው ገዢ ቡድን ነፃ መሆን አለበት። ከዚህ ገዢ ቡድን ለሚሠነዘሩ አዘናጊ ፍርፋሬዎችና ማስፈራሪያዎች፤ ቆራጥ፣ ፈጣንና፣ የማያወላዳ የተቃውሞ መልስ መሥጠት አለበት፤

፲፬ኛ. ምን ጊዜም ቢሆን የእንቅስቃሴው ትኩረት፤ ከግቡና ከትክክለኛ ሂደቱ ለአንዲት ሰኮንድ መዛነፍ የለበትም፤

፲፭ኛ. ይህ እንቅስቃሴ ነቅቶ መጠበቅ የሚያስፈልገው፤ የወያኔ አይቀሬ ውድመት ሲመጣ፤ አሁን አንገታቸውን ደፍተውና እውነተኛ ፊታቸውን ደብቀው፣ አድፍጠው ይቺን ሰዓት የሚጠብቁና ራሳቸውን በሥልጣን ላይ ለማቆናጠጥ ከሚፈልጉ፤ የሕዝብ ፍላጎት ሣይሆን የራሳቸው አጀንዳ ከሚመራቸው ሽማቂዎች ነው፤

ተዘጋጅተናል። ትግሉ ያለማንም ግለሰብ ፍላጎትና ውሳኔ፤ በተጨባጩ የሀገራችን የፖለቲካ ሃቅ ተመርኩዞ ይቀጥላል። አለሁ ባይ አለሁ ይበል።